Aurora Public Schools

**Division of Equity in Learning**
15751 E. First Ave.
Aurora, CO 80011

Phone – 303-340-0859
Fax – 303-326-1966
Web – auorak12.org

**ፌብሯሪ 2018**
**የሥርዓተ-ትምህርት ዝመና—የመጀመሪያ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ማንበብና መጻፍ (ሊትረሲ)**

የAPS ማንበብና መጻፍ (ሊትረሲ) ቡድን የማንበብና መጻፍ (የሊትረሲ) መማር-ማስተማር ሁሉንም ክፍሎች ለመደገፍ የተለያዩ የርከን 1 (Tier 1) ግብዓቶችን/ሀብቶችን ለመገምገም እና ለመደገፍ በሴፕቴምበር 2017 ውስጥ ግብረ-ኃይልን አዋቅሯል። የግብረ-ኃይሉ ዓላማ መጻፍን እና ቃላት ማጥናትን የሚደግፉ የተለያዩ ግብዓቶች/ሀብቶች ወጭ ትንተናን ለዲስትሪክቱ አመራር ቡድን ማንበብን መስጠት ነበር። ቡድኑ የተመጣጠነ የማንበብና መጻፍ (የሊትረሲ) መማር-ማስተማርን በመደገፍ ላይ ለኮሎራዶ የትምህርታዊ ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) በተሻለ መልኩ የሚስማሙት የትኞቹ ግብዓቶች/ሀብቶች ናቸው የሚለውን ለመወሰን በተለያዩ አቅራቢዎች የተሰጡ አቅርቦቶችን በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተከታትሏል። የግብረ-ኃይሉ አባላት የት/ቤት አመራሮችን፣ በማኅበረሰቦች በሞላ የማስተማር አጋሮችን፣ ክልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ከባህልና ቋንቋ ብዝሃነት ትምህርት ውክልና ያለው የAPS የማንበብና መጻፍ (የሊትረሲ) ቡድንን ያካተተ ነው።

በመጀመሪያው ግምገማ ጊዜ የሚከተሉት የሥርዓተ-ትምህርታዊ ግብዓቶች/ሀብቶች ተገኝተዋል፦

| ርዕስ | አሳታሚ | ደረጃ | አስተያየቶች |
|---|---|---|---|
| Fountas and Pinnell *Classroom* | Heinemman | መጀመሪያ ደረጃ | • በወቅቱ የተስማሙና ጥቅም ላይ ያሉ ማቴሪያሎች የዘመኑና አዳዲስ ክፍሎች<br>• ለማስማማትና ጥቅም ላይ ለማዋል በመገምገም ላይ |
| Teachers College *Reading and Writing Units of Study* | Heinemman | መጀመሪያ ደረጃ | • በአሁኑ ጊዜ በበርካታ የAPS የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በጥቅም ላይ ያለ፤ ለማስማማትና ጥቅም ላይ በማዋል /adoption/ ሂደት ውስጥ አላለፈም<br>• ለማስማማትና ጥቅም ላይ ለማዋል በመገምገም ላይ |
| *Wonders* | McGraw Hill | መጀመሪያ ደረጃ | • ጥቅም ላይ እንዲውል ለመምከር በግምገማ ላይ<br>• የ16 መማሪያ ክፍሎች መምህራን *Wonders* እና *Benchmark Advance* ሁለቱንም በመገምገም ላይ ናቸው |
| *Benchmark Advance* | Benchmark | መጀመሪያ ደረጃ | • ጥቅም ላይ እንዲውል ለመምከር በግምገማ ላይ<br>• የ16 መማሪያ ክፍሎች መምህራን *Wonders* እና *Benchmark Advance* ሁለቱንም በመገምገም ላይ ናቸው |
| Teachers College *Reading and Writing Units of Study* | Heinemman | መካከለኛ ደረጃ | • በአሁኑ ጊዜ በበርካታ የAPS የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በጥቅም ላይ ያለ፤ ለማስማማትና ጥቅም ላይ በማዋል /adoption/ ሂደት ውስጥ አላለፈም<br>• ጥቅም ላይ እንዲውል ለመምከር በግምገማ ላይ |
| ARC | የአሜሪካ የንባብ ኩባንያ /American Reading Company | መካከለኛ ደረጃ | • ጥቅም ላይ እንዲውል ለመምከር በግምገማ ላይ |
| EngageNY | EngageNY | መካከለኛ ደረጃ | • ጥቅም ላይ እንዲውል ለመምከር በግምገማ ላይ |

በግምገማ ላይ ያሉትን ግብዓቶች/ሀብቶች ግምገማቸውና አስማምቶ ለመጠቀም የማረጋገጡ ሂደት በማርች አጋማሽ እንደተጠናቀቀ የእነዚህ ህትመቶች የመምህራን እትም እና የተማሪ እትም በሙያዊ የትምህርት ኮንፈረንስ /Professional Learning Conference/ ማእከል፣ 15751 E. 1st Ave, Aurora CO፣ ከማርች 19 እስከ ማርች 30 ከ7:30-3:00 ድረስ ለእይታ ይቀርባሉ፣ ጎራ ብለው ግብዓቶቹን/ሀብቶቹን እንዲነቡኙ እና አስተያየቶችን እንዲሰጡ ግብዣየን አቀርብልዎታለሁ። ስለግብዓቶቹ/ሀብቶቹ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት በቅርብ ከሚወጡ ግብዓቶቹ/ሀብቶቹ በAPS የመማሪያ ክፍሎች በተግባር የሚታዩባቸው የቪዲዮዎች አገናኞች ጋር አገናኝ ይጫኑና ይመልከቱ።

Starla Pearson

ዶ/ር ስታርላ ፒርሰን /Dr. Starla Pearson/
የመማር እና ማስተማር ሂደት ዳይሬክተር